የሻለቃ ዘውዱ ስኳሬ

በተመስገን ገብሬ

የንቅናቄ ጽንሰ ሐሳቡና መጽሐፉ በነቁ ወጣቶች በመሳ መንግሥቱ ለተቀሳሚዎቹ ንቃተ ሥላሴ

ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ኦዳስ አበባ ግቢ ሚሽሌ ሳ ሳ

ብሔራዊ ማተሚያ ቤት ታተመ

ክፍል ፩ ።

በጉለሌ የነበረው የታወቀ ዶሮ ነጋዴ ማነው ብለው ከገፈ ርካ እስከ ደጃዝማች ይገዙ ሠፈር ለጠየቁ ሰዎች ፡ ተበጀ ፡ ሰካ ራሙ ተበጀ ፡ ዶሮ ነጋዴው ተበጀ ፡ ነው ብለው ይነግርዋቸዋል ።

የሕይወቱ ታሪክ ፍጹም ገድል ነው ። ጠም ያለው ሽማግሌ ሰው ነው ። የራሱን ጠጉር ወዛ ወይም መቀስ ነክቶት አያውቅም ። ማለዳ አይናገርም ። በጠርሙስ የከመረውን ከጠጣ በኋላ ማታ ሲራ ገም ወይም ሲሳደብ ፡ ሲፈክር ፡ ወይም ሲያቅራራ ድምጡ ከፈረ ንጅ ውሽ ድምጥ ይወፍራል ። ቢያውቀውም ባያውቀውም ላገ ኘው ሁሉ ማታ ሰላምታ ይሰጣል ። ቢያወቀውም ባያውቀውም ካገኘው ሁሉ ጋራ ማታ ይስታል ። ቢያወቀውም ባያወቀውም የሰ ላምታው ዓይነት እንደወታደር ወይም እንደሲቪል ቢሆን ለእርሱ እንደተመቸው ነው ። ከሰላምታው ጋራ ድምጥ ትሰማላችሁ ። ከአፉ ከሚወጣው ግን አንድ ቃል መለየት አትችሉም ።

ቦን በተፈላ ጊዜ በጉለሌ በየምድጃው ሥር የሰካራም ተረት የተጫወተው ሰው ሁሉ የተናገረ በተበጀ ላይ ነው ። መልኩን አያተ ውት ያላወቁ ባልቴቶች እንኳ ከጥንጃል ቡናን ፉት እያሉ የሌ ላውን ሰካራም ተረት በተበጀ ላይ ይላክኩት ነበር ። ይህ እው ነት ነበር ። በጠባዩ ከተባለበት የባሰ ሰካራም ይሁን ወይም የተ ሻለ ከጉለሌ ባሕር ዛፍ ውስጥ ወጥቶ አንድ አዲስ እንግዳ ሰው ሁኖ ለአዲስ አበባ ታይትዋል።

ከዱሮው የእንጨት ጉምሩክ አጠገብ ወደ ምሥራቅ ሲል ካለው መንገዝ ማዶ ድልድዩን ወደ ምሥራቅ ተሻግሮ መጀመሪያ የሚ ገኘው አነስተኛ ሳር ክዳን ቤት የተበጀ ቤት ማለት ያ ነው ። በዚያው በቤቱ በዚያው በጉለሌ በሠፈሩ ኖረ ።

እንጨቱን ተሸክሞ አፈሩን ቆፍሮ ቤቱን የሠራው እርሱ ነው ። ዋጋ ከፍሎ አስከድኖታል ።

ተበጀን ኩራት ተሰማው ። ቆይቶ ደግሞ ዓይኖቹ እንባ አዘሉ ። በጉንጩም የእንባ ዘለላ ወረደው ። በግራ እጁ መዳፍ ከጉንጩ የተንከባለለውን እንባ ጨፈለቀው ። ዓይኖቹ እንባ ያፈሰሱ ለራሱ ኀጢ ስላለው ነው ። ሊነገር በማይቻል ደስታ ልቡ ተለውስዋል ።

ዝናም ያባረራቸውም ከቤቱ ጥግ ሊያጠልሉ ይችላሉ ። ቤት የእግዚአብሔር ነውና ወኾኅብ እንዳያገኛቸው ከቤት ውስጥ ዝናሙ እስኪያባራ ይቆያሉ ። ተበጀን « ቤትህን ይባርክ » ሊሉት ነው ። እንግዲህ መንገደኛው ሁሉ " ይህ የማን ቤት ነው ? ብሎ ሲጠይቅ የተበጀ ሊባል ነው ,, አለ ።

ቀጥሎ ደግሞ « ተበጀ የጎኖው ነው ሲባል ዶሮ ነጋዲው ሊባል ነው » አለ ።

« ዶሮ ነጋዲው የትኛው ነው ሲባል ያ የጉለሌው ሰካራም ሊባል ነው ። አወይ ! እኔ ተበጀ ፤ ተበላሽቻለሁ » አለና ደነገጠ ። ከዚህ በኋላ ስለ ቤቱ ክብር እንኳ መጠጥ መተው ይገባኛል አለ ።

መጠጥ ለመተው ያሰበበት የመጀመሪያ ጊዜው ይህ ነው ። ሰካራምነት ጉዳት መሆኑ ተሰምቶት እንደሆን ይናገር ስለ ቤት ክብር ግለቱ ግን ወደ ጎር ይቆይ ። ስለ ቤት ክብር ምን ያውቃል ? ዶሮ ነጋዲው ተበጀ ሰካራሙ ተበጀ አይደለምን ?

ሰካራሙ ተበጀ የሠራውን የገዛ ቤቱን ከፍቶ ገበና ኩራዙን አስቀምጦ ክብሪቱን ለመጫር ሲያወጣ በሐሳብ ተሰቅዘ እንደዚህ አሰበ ። መምረጥ አለብኝ ። ከዚህ ቤት ያለው መጠጥ ሁሉ አንድ ሳይቀር እየወጣ ይፍሰስ ፤ ከዚህ በኋላ ክብሪቱም ኩራዙም በቤት ይደር ፤ በአዲሱም ቤት ብርሃን ይዙርበት ። አለዚያም በአዲሱ ቤት መጠጥ ይዙርበት ፤ ኩራዙና ክብሪቱ ከቤት ይውጣና ይፍሰስ ። ሊደረግ የሚገባ ከሁለቱ አንዱ ነው እንጂ ፤ በሰካራሙ ተበጀ ቤት መጠጥና እሳት በአንድነት ይህች ውሽት አለና ሳቀ ።

ከሁለቱ አንዱን ለማድረግ ሳይቆርጥ መብራቱን አቃጠለና ተቀመጠ ። እንደገና ደግሞ እንደዚህ አሰበ ። አያድርገውና ዛሬ


ሰክሬ ይህ ቤት ቢቃጠልብኝ አመዱን አይቶ በሰከራሙ ተበጀ ላይ ለመሳቅ ድፍን ጉለሌ ነገ ከዚህ ነው የሚቆም ! ጉለሌ ምን ባለኝ ? ወሬ ከማበክት በቀር ጉለሌ ምን ሥራ አለው ? ለአዲስ አበባም የስድስት ወር መሳቂያ በሆንኩ ነበር ። መንገድ አላፊ ዎችም ነገ በዚህ ሲያልፉ አመዱን አይተው ይህ የተቃጠለው ቤት የማን ነበረ ሲሉ የተበጀ ሊባል ነው ። በሰካራሙ ተበጀ ቤት መጠጥና እሳት በንድነት ይህች ውሽት !

ወደ ውጭ እንደ እርም ወረውሮት የነበረውን የመጠጥ ጠርሙስ ሁሉ በጨለማው ዳብሶ አንድ በአንድ ለቃቀማቸው ። አንዱን ግን ቀና አደረገና ከአፍንጫው አስጠግቶ አሸተተው ። በጠርሙሱ ቅርፅ የመጠጡን ዓይነት አወቀው ። ዊስኪ ነበርና ስለ ዚህ ነው ሰው እንዳይሰማ ቀስ ብሎ የሳቀ ። የጠርሙሱን ግማሽ ከጠጣ በኋላ ግን በአፉ ቡሽ ቢወትሩበት ለሳቁ መጠን የለውም ።

« ጉለሌ ተኝቷልና ከዚሁ ከባሕር ዛፍ ሥር ቁጭ ብዬ ብጠጣ የሚታዘበኝ የለም » አለና አሰበ ። እውነቱን ነው ። ጉለሌስ ተኝቶ ነበር ነገር ግን አሁን እርሱ ጠጥቶ የሰከረ እንደሆን ጉለሌን ሊቀሰቀሰው ነው እርሱ ከጠጣ በጉለሌ ውስጥ ማን ይተኛል ?

ጠርሙሱን ከከፈተው በኋላ ብርጭቆ ያስፈልገው እንደነበረ ትዝ አለው ። ሶስት የሚሆን ደጎና ጉንጭ ጠርሙሱን ከአፉ አስ ጠግቶ ጨለጠ ። ከዚያ በኋላ የሚጠጣበት ብርጭቆ ሊያመጣ አሰበ ከዚያ በኋላ ደግሞ በሶስት ጉንጭ ምን ያህል ጠርሙሱን እንዳጉደለው ለማወቅ ጠርሙሱን ቀና አድርጎ በጨረቃዋ ተመ ለከተ ። « ግማሹን ያህል ሰርጕጀዋለሁ » አለና በሳቅ ፈነዳ ። « ለዚችስ ብርጭቆ ማምጣት አያሻም» እያለ ጠርሙሱን አምበ ሮበጨው ። በቀኝ ክንዱ መሬቱን ተረክዘ የቀረውን ጅው አድርጎ ወደ ውስጥ ጣረወረው ። በዶውን ጠርሙስ ደግሞ በጁ እየጠነ ቆለ « አንተን ደግሞ ለአንድ ዶሮ ለውጬ ሞያ አስይዝሃለሁ የዊስኪ ቅርፍቱም ዋጋ አለው አይጣልም » አለ ።

‹ እንዲሁ ሲጠጣ ሌሊቱን አጋመሰው ። ቀጥሎከእግሩ በታች የመ ደቀውን ጠርሙስ እየቆጠረ ይህን ሁሉ እንደጠጣሁት አላምንምና በጉ ለሌ አፈርሳታ ይደረግልኝ እነናቂ እነተሰግ አገቱም ይጠጣሉ› አለ ።



የጠርሙሱ መጠጥ ሁሉ እስኪያልቅ ድረስ ከዚያው ከዛፉ ሥር ተቀምጦ ያን ጠንካራ ትምባሆውን ከአፉ አለየውም ። በሳቀ ጊዜ ብቻ መልሶ ገም እስኪል ድረስ መጠጡ ወይም ትምባ ሆው ከአፉ ያቋርጣል ። የመጠጥና የትምባሆ ጊዜው ተበጀ ይህ ነው ።

ግለዳ በቀዝቃዛ ውሀ ታጠበ ። ቋንጣም እንቁላልም ጠበሱ፣ በዳቦ በላ ። የጠም ቀን ነበር ‹ ለአባ ተክለ አረጋይ አልናገርምና ነፍሴ ሆይ ግድ የለም › አለ ። የነፍስ አበቱን ማለቱ ነው ። ምና ልባት በዓመት እንኳ አንድ ጊዜ ጠይቋቸው ወይም ጠይቀውት

አያውቁም ፣ እርሱንም አያደርሰውም ፤ እርሳቸውም ከበዓታቸው አይ ወጡም ፤ አንዳንድ ጊዜ የዛሬውን እሑድ ፅረፍት አደርገዋለሁ ያለ እንደሆነ እግሩን ደኅና አድርጎ የሚታጠብበት ቀን ማለት ነው ።

ደክሞት ነበርና ደኅና እንቅልፍ ተኝቶ ነበር ። ዝናሙን ሄዱ ድንዱን ጐርፉን ውሀ ምላቱን አልሰማም ። አንዳች ነገር ሰማ ። ዘፈንና እልልታ የሰማ መሰለው ። ትናንት ከጠጣው መጠጥ ኃይል መሰለውና ይህስ ሰብደት ነው እንጂ ስካር አይደለም አለና ተመ ልሶ ተኛ ።

እንደገና አዳመጠ ። የእርዳታ ጥሪ ጩኸት ሰማ ። ከአልጋው ዘልሎ ከወረደ በኋላ ቤቱን ለመገጋት ጊዜ አላገኘም ። በትልቁ ወንዝ ዙሪያ ቁመው ይጮሁ የነበሩ ሰዎች የውሀው ምላት የሾ ገሌን ገረድ እንደጠለፋት ነገሩት ። ጐርፍ የወሰደው ሾገሌን ራሱን ቢሆን ወይም የሾገሌን ገረድ ለተበጀ ማዕርግ ምኑም አይደለም ።

‹ ገረዲቱን እናንተ በመጨረሻ ያያችኋት ወዴት ነው ? › ብሎ ጠየቀና እየጠለቀ በዋና ይፈልግ ጀመር ። ስለሾገሌ ገረድ በትኩስ ውሀ ምላት ለመግባት አንሠዋም ያለው ጉለሌ በዳር ተሰልፎ ቁሞ ተበጀን ይመለከት ነበር ።

ብዙ ጠልቆ ከቆየ በኋላ ብቅ አለና ‹ አገኘኋት መሰለኝ › ብሎ በዳር ላሉት ጮሆ ተናገረ ። ለሰው ሁሉ ደስታ ሰጠው ። ከሁሉም ይልቅ እርሱን ደስ አለው ። የጠለቀውና የዋኘው ረጅም ጊዜ ስለሆነ ደክሞት ነበር ። ነገር ግን ሊያወጣት ይገባዋል ። ጠለ ቀና አገኛት ። በአሸክሙ ላይ ጥበብ ያስፈልጋል ። አለዚያስ ውሀው ምላት እንደገና ይነጥቀዋል ። እንደተሸከማት ውስጥ ለውስጥ ዋኘና ከዳር ብቅ አለ ።

ክሸክሙ ክብደት ኃይል የተነሣ ወዲያው ወደቀ ። እርዳታ ተነ ባበሩለትና ገላቱው እርሱንም እርሷንም አወጧቸው ።

ተበጀ ተንዘራግቶ በብርቱ ውጋት እያቃተተ የጉለሌ ሰው በሳቅ ሲፈነዳ ሰማ — ከራሱ በኩል ቀና አለና ‹ ሴትዮዋ ድናለች ? › ብሎ በርኅራኄ ደምዕ ጠየቃቸው ።

ሁለተኛ ክፍል ።

ከሚያሰክር ሁሉ ትጎርምተኛ ለመሆን ብዙ ጊዜ አለፀ ነበር ። ሰክሮ ያደረበት ሌሊት አልፎ ብርሃን በሆነ ጊዜ ከእንግዲህ ወዲህ «መጠጥ አልቀምስም» እያለ እየቀኑ በብርሃን ተበጀ ምልዋል ። በነጋው የበለጠ ጠጥቶ የባሰ ሰክሮዋል ። ለመስከር ይጠጣል ። ደስ ያለው እንዲመስለው ይጠጣል ። ብስጭቱን የሚረሳ መስሎት ይጠጣል ይህ ነው ተበጀ ።

« ይህን መስከርህን ካልተውህ ላንተ አበ ነፍስ አልሆንህም » ብለው የመጀመሪያ ንስሐ አባቱ ብዙ ከመከሩት በኋላ መንፈሳዊ ልጅነቱን ከርግመት ጋራ አስወግደውታል ።



ገረዶቹም ለርሱ ተቁጥሮ ሙሥራትን ከሙርደት ቆጥረውት እየነቀፉት ሄደዋል ። « መጠጥ ከልተውህ አናገባህም » ብለው እየ

አንዱ ቀረበና አሳማ ነው ያወጣሃው አለው ።

የሚያቃትተው ተበጀ ከወደራሱ ቀና አለና « አሳማ ? » ብሎ ጠየቀው ። «ለመሆኑ ከእናንተ ውሀ የወሰደባችሁ ሰው ነበር ወይስ አሳማ ኑርዋል ? » ብሎ ተበጀ ጠየቀና ያቃትት ጀመረ ።

ጎረቤትህን እንደነፍስህ ውደድ ቢባልም ሰዎችን እነ እቲላን ነበር እንጂ የእቲላን አሳማዎች አልነበረም ። እቲላ ጎረቤቱ አሳማ እርቢ ነው ። ውሀው ምላት ነጥቆ ወስዶ የነበረ የእቲላን አሳማ ሳለ ያላዩትን ቢያወሩ ግድ የሌላቸው ሰዎች የሾገሌን ገረድ ውሀ ወሰዳት ብለው አውርተው የተበጀን ነፍስ ለአንድ አሳማ ነፍስ ሊያስለውጡት ነበር ።


መልካሙ የሰማዕትነት ሥራው ሁሉ ደግሞ እንዲሁ ርካሽ ሆኖ የሚቆጠር የሆነበት ዘወትር የሚሰክር ሆኖ ስለታወቀ ነው ። በሞራልም (ግብረ ገብነት) መሠረት አደረግሁት የሚለውን ሁሉ ሳያጨቀው እንደሚያደርገው ይቆጥሩበታል ። «በጎ ሥራህን ሁሉ በትኩስ መቃብር ውስጥ አፈር አልብሰው አንተ ሰው ሁን ሚስት አግበ ልጆች ይኑሩህ» ይሉና ይዘልፉት ነበር ።

ድኃ ቢሆን ወይም ባለጠጋ ሰካራም ቢሆን ወይም ትጎርም ተኛ ሁሉም የጉለሌ ልጆች ነን አባታችንም ጉለሌ ነው ብሎ ራሱን የሚያከራ እርሱ ተበጀ ብቻ ነበር ።

ጊዜው ለጋብቻ ጠይቋቸው የነበሩ በቁመናው አሰናብተውታል። በሰ
ምቤቱም በማኅበርም መኅበረተኛ ለመሆን የጠየቃቸው ነፍሱን
ሳይቀር ንቀዋታል።

ይህ ሁሉ በእርሱ ዘንድ ከኢምንት አይቆጠርም። ያሉትን ቢሉ
እርሱ ምን ቸገረው፤ ገንዘብ እኮ አለው፤ ገንዘቡም ጥሬ ብር ነው።
ባለጠጋ ነው። መስከርም የባለጠጎች ነው። ትኅርምተኛ መሆንም የድ
ሆች ነው። እንደልዩ ዓመፅ አድርገው ለምን በእርሱ ይቆጥሩበታል?
እንዲህ በተከራከረ ነበር።

ነገር ግን ልዩነት አለው። እርሱ ብዙ ጊዜ ሰክሮ አቶሞ
ቢል በላዩ ላይ ሐዲበታል። ሰክሮ በበነጋው ከእንቅልፉ ሲነቃ
ብዙ ጊዜ በእስር ቤት ውስጥ አድሮ ራሱን አግኝቶታል። በጉ
ለሌ መንገድ ዳር ባሉት በብዙ የውሀ ጉድጓዶች ሰክሮ ገብቶ



ባቸው እየተጮኸ ጉለሌ አውጥቶታል። ሰክሮ የጐርፍ ውሀ ከመ
ሰደው በኋላ ብዙ ጊዜ የእሳት አደጋ ደርሶለታል። ሰክሮ ከቤቱ
መድረስ እያቀተው ከወደቀበት ባቡር መንገድ ሳይነሳ ብዙ ጊዜ
ጐርፍ በላዩ ላይ ሲሔድበት አድርዋል።

ይህ ሁሉ ውርደትና ርክሰት ነው እንጂ ክብር ከቶ አይ
ዶለም። እንግዲያስ ክቡር ደሀ ነው። ገንዘብ ስለሌለው፤ ራሱን መግ
ዛት ይችላል። ባለጠጋ ደግሞ መናኛ ተራ ነው። ገንዘብ ስላለው

ራሱን መግዛት አይችልም። ይህን ሁሉ አስበ። ስለኖረ ባያማር
እንኳ ብዙ ከግወቅ ደርስዋል። «ባለጠጋ ሆነ ወይም ደሀ፥ ሰው
ከራሱ የበለጠ መሆን ይገባዋል» አለ።

ቤቱን ከሠራ ከአምስት ወራቶች በኋላ ጀምሮ ተበጀ መጠጥ ከቶ
አልጠላም ስለቤቱ ክብር መጠጥ እርም ነው ማለት ጀምሯል። ያለ
ፈውንም ዘመን መራርነት እያሰበ ተንገፍግፍዋል። አንድ ብሎ ለመጀ
መር ከወደቀበት ትብያ አንሥቶ ዕድሉን ሲያራግፍ እንደ ራዕይ ያያል።

ያበላሸው ዕድሉ አሳዘነው «በዚህ ዕድሜዬ ሁሉ ሚስትም
አላገባሁም ልጅም የለኝም» አለና አዘነ። ውሾቹ እየተባሉ ሲጫ
ወቱ ተመለከተና «አመሌ ውሻ ነበርና ከውሾች ጋር ኖርው» ብሎ ራሱን ረገመ። በውሾቹ ፈንታ አሁን በዚህ ዕድሜው ልጆቹ
ዙርያውን እየተሰባሰቡ ሲፈነፍጉ ባየ ነበር እንዲሁ አሰበ።

ቀልድና መዘበራበት ስለሚያውቅ እንደዚህ እያለ ይቀልድ ነበረ።

«ጐጃም የአበባውንና የግራር ማሩን ይሊሳል። የተጉለትና
የአምቦ ወረዳ ጌሾውን ያቀርባል። የሆላንድ የቢራ ፋብሪካ ቢራ
ውን ያወጣል የኢጣልያ ፋብሪካ ወይን ጠጅ (ነዚት) ያፈላል።
መደቅሳና ዘቶስ በግሪክ አገር ይጣራል በስኮትለንድ ዊስኪ ይጠ
መቃል። ይህ ሁሉ የሚደረገው በአራዳ የሚቀመጡትን እንጸያ
ጠግቸው ነው። በዚህም ምክንያት በዋሽዋ እንደምትሬሀ ጉንጉት
ሰካራሞች በከተማይቱ ይርመሃሉ።

«በደብረ ሊባኖስ ግን ድምጡን ዘለግ አድርጎ የሚናገር
ሰው እንኳ የለም። ውሃ እንኳ የሚጠጣ በመቅኑን ነው። በአ
ራዳ ይሁን ወይም በገዳም ምንም ገንዘብና ቢስቲን ለሴለው፥
ወሀ ደግሞ እጅግ አድርጎ ይጣፍጣል።» ይህን የመሰለ ቀልድ
ይቀልድ ነበረ።

ሰካራሙ ተበጀ ግን ገንዘብ እያለው ወሀ ጣፍጠታል። ልዩ
በሆነው በዚያ ማታ ወደ አልጋው ሰውዩ በተኛ ጊዜ መጠጥን
እርም ካደረገው አንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ከዘጠኝ ቀን አንደ
ሆነው ጊዜውን ቆጥሮ አወቀው። ጊዜውንስ ማወቅ ለምን አስፈለ

ነው ! «እንደ ጉድፍ (ጥንብ) መጣያ ትንፋሽ ተበላሼ ፤ አፈም እንደ እሬት መረረኝ ፤ ሹልክ ብዬ ፤ ዛሬ ብቻ ፤ ጥቂት ብቻ ፤ አንድ ጊዜ ብቻ ፤ እኔ ብቻ ፤ ብጠጣ ምን ይገዳል » ብሎ ተመኝቶ ስለነበረ ነው ። ነገር ግን ወደ አልጋው ወጥቶ ተጋደመ ከተጋ ደመም በኋላ ተነሥቶ ወደ መጠጥ ቤት ለመሄድ ከባድ ከነበረው እንቅልፉ ለመላቀቅ ታገለ ።

በመጨረሻ ወደ መጠጥ ቤት በሄደ ጊዜ በውኑ ወይንም በሕልሙ እንደነበረ ራሱም ተበጀ አላወቀውም ።

የጠጣም እንደሆነ ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ይደረግ በነበረው የአረመኔ ቅጣት እጁና እግሩ ከመቆረጥ ይደርሰል ብሎ አላሰበም ። አናጢ የጠረበው እንጨት ከቅልጥሙ ይቀጠላል ብሎ ክፉ ሕልም አላለመም ። አንድ ሰካራም አንካሳ በአንድ ዓመት ስንት የእንጨት እግር ይጨርሰል ብሎ ስለዋጋው አልተጨነቀም ። ደኅና ምኞት ያለው አንካሳ ለመሆንም ገንዘብ ያስፈልጋል ።

አንካሳው ሰው ሰካራም እንደሆን በእንጨት እግሩ በሰላም ጊዜ ይሄድበታል ። በሁከት ጊዜ ደግሞ ይጣታበታል ። ሲጣታበት ይሰበራል ሲሰበርም ሌላ የእንጨት እግር መግዛት ያስፈልገዋል ። ስለዚህ የእንጨት እግር የሚሠሩ አናጢዮች ለደንበኞቻቸው ትርፍ መጠባበቂያ እግር በሜንጦ ሰቅለው ያስቀምጡላቸዋል ይባላል ። ተበጀን እንደዚህ ያለ ሕይወት አያጋጥመውም ።

በበቀለች ዓምባዬ መጠጥ ቤት ደረጃውን ተራምዶ ተበጀ በገባ ጊዜ የጥንት ወዳጆቹ ሰካሮች በእቅፉ ላይ ተነባበሩ ። እን ደተወደደ መሪ በጫንቃቸው ላይ ተሸክመው እየተቀባበሉት በዕልልታ ጮሁ ። ከመጠጥ ቤት ጠፍቶ የነበረው ተመልስዋልና በሰካሮች ሁሉ ዘንድ ደስታ ሆነ ። እንኳን በደኅና ገባህ ! የመጠጥ ጠርሙሶቹን እንደ ዘንባባ ይዘው ተቀበሉት ቁማርተኛው ያረጀ ግሪክ እየሳለ ተናገረ ሁሉም በደስታ ይጮሁ ስለነበረ አንድም የሰማው የለም ።

ረስቶት የነበረውን መጠጥ ጣዕሙን ገና ሳያወጣቀው ገና ከጫንቃቸው ሳይወርድ በጩኸቱም በመጠጡም ተበጀ ሰከረ ። ከጫንቃ ቸው ወደ ቁልቁል ጣሉት ። የሕፃንነትህ ዘመን አልፏልና ራስህን ችለህ መሄድ ይገባሃል አሉት ። ሰማህ ? አቅም አንሰህ መ አቅቶሃል እንደኩብኩባ እየዘለልህ መሄድ ትችል እንደሆነ ምር ይኸውልህ ብሎ አንካሳው በየነ አቀበለው ። ምርኩዙን ለመያዝና ጨበጥ እጁን ሲዘርር በግምባሩ ከመሬት ላይ ተደፋ ። እንደ ቀም ሳለ ፤ እስኪነቃ ድረስ በመካከሉ ስንት ሰዎች አልፎ እ ነበረ ለማስተዋል አልቻለም ።

የመጠጥ ቤቱ እመቤት ጊዜ አልፎአልና ከውጭ ጣሉት ቤቱን ዝጉት ብላ አዘዘች ።

ወደቤቱ የተመለሰ መሰሉት ሄደ ። ግወቅ አልቻለምና ወዲ እንደሄደ ግን አላወቀም ። አንድ መንገድ ሲያቋርጥ ተሰናከለ ወደቀ ። ከወደቀበትም ምድር ላይ በዳሰሰ ጊዜ ለእጁ የገጠመው የባቡሩ ሐዲድ ነው ። ቤቱ ያለ በጉለሌ ነው ። የሰከረበት ደግሞ የበቀለች መጠጥ ቤት ነው ። መጠጥ ቤቱም ከሦሐንስ ቤተ ክር ስቲያን አጠገብ ነው ። ምን ያህል ቢሰክር ነው የጉለሌ መንገድ ጠፍቶት እስከ ባቡር ሐዲድ ድረስ ተሳስቶ የሔደ ? ራሱን ይ ለመርሳትም ራሱ ወዴት እንዳለ ማወቅ አቃተው ። እንደ ቤተ መንገድ ጠፋበት ።

ጥቂት መስዓት ከቆለ በኋላ ጨዝት በስቶ ኋላው ይነ የነበረ የእሳት አደጋ ወይስ ባቡር ኑሮዋል ? አያፍደፍደ ሲሔደ ከወደ ኋላው በኩል ምን እንደገፋው አላወቀም ፡ ከኋላው በኩል ትልቅ ኃይል መታው ፡ ከፊቱ በኩል የቀበሮ ጉድጓድ ተቀበለው ፡ እግሩ እንደ ብርጭቆ ነከተ ። ከወደቀበትም ሌሊቱን ሁሉ ደም ከእግሩ ዘነመ ። ትንሻም እንደ ንብ በላዩ ሰፍሮ ደሙን መጠጠው ።

ቀና ብሎ በአጠገቡ የወደቀውን የአህያ ሬሳ አሞራዎች ሲ ጡት አየ ። የቀረው ልቡ በደንጋጤ ተመታ የእርሱ ዕድል ከአህ ያው ሬሣ ዕድል ቀጥሎ ሆነ ። በስካሩ ምክንያት እስከ ዘላለም ድረስ ከአህያ ሬሳ እንደ ማይሻል ተረዳው ። ነገር ግን የአዞን መረዳት ለምን ይበጀዋል ? ግወቅ የሚያሰፈልግበት ጊዜ አልፏል ።

በሕይወቱ ሳለ እንደ ወደቀ ያህያ ሬሳ መነሣት አልቻለ ምና በተራው አሞራዎቹ ዓይኑን ሊመነቁሩት ነው ።

ተው ከጨረሱት በኋላ አጥንቱን ሊግጡት ነው ። ሌሊት ደግሞ ቀበሮዎች ሊረፋረፉበት ነው ። ይህን እንዳያመልጥ ለመሸሽ ከወደ ቀበት ሊነሣ እያቃተተ ሞከረ ። ባልተጠለጠ ጊዜ ግን ተጋደመ ።



በደሙ ላይ እንደተጋደመ አራት ቀኖች አለፉ ። እግሩ እንደ ቀርበታ ተነፋ ። እንደ ቅጠልያ ያለ እኽ ወረደው ። ከወደቀበት ያን ማው የመንግሥት አምቡላንስ ባገኘው ጊዜ ፈጽሞ በስብሶ ነበር ።

ዶክቶር ክሪመር ባዩት ጊዜ ከሰማይ በታች ሊደረግለት የሚ ችል ሕክምና ምንድር ነው ? ደሙ አልቀዋል ። በሽተኞችን ለመ ርዳት በጎ ፈቃድ ካላቸው ሰዎች የተለገሠውን ደም ለሚሰክር ጥጋ በኛ አልሰጥም ። እርሱን መንካትም መርዙ ያስፈራል ከዚህ በፊት ይህ እንዳይደርስበት እንዳይሠክር ብዙ አስጠንቅቀነው ነበር አሉ ።

ከንፈሩ ተንቀሳቀሰ ። ላብ በፊቱ እንደወደ ፈሰሰ ። ለመናገር ጣረ ። በመጨረሻ ግን መናገርም ሳይሆንለት ቀረ ።

ሐኪሞች የገማውን ልብሱን ገፈፉት ። እንደቅርጫም ያለ መጽ ኃኒት ቀቡት ። ከግማሽ ሊትር የበለጠ ደም ሰጡት ። በመጠጥ ኩቱ ገጸው ከልቡ ደክም የተነሣ ኤተር ለመቀበል አለመቻሉን በተ ረዳ ዘንድ የሚያፈገፍ መድኃኒት ጀርባውን ወግተው ሰጡት ።

አንዱ ሐኪም ከገልበቱ ይቆረጥ አለ ።

ሌላው ግን ሁለተኛ እንዳሰክር ከቂጡ አስጠግቼ እቆርጠዋለሁ አለና ከቂጡ አስጠግቶ ቆረጠው ። የተቆረጠውን እግሩን ከፊቱ መዝ ናችሁ አስታቅፉት ብሎ አስታማሚዎችን አዘዘ ።

እግሩን ከፊቱ መዘኑትና አሥር ኪሎ የሆነው እግርህ ይኸ ውልህ ታቀፈው ብለው አስታቀፉት ።

በዚህ ጊዜ በአጥንት የተጣሉት ውሾች በላዩ ላይ ተረፋረ ፉብትና በድንጋፂ ከእንቅልፉ ነቃ ። ይህ ሁሉ የደረሰበት በሕልሙ እንደነበረ ማወቅ አቃተው ። ከአልጋው ላይ ወረደና ገረዱን ወይ ዘሮ ጥሩነሽን ከመኝታቸው ቀስቅሶ እየጮኸና እየተንዘረዘረ ስንት እግ ነው ያለኝ ብሎ ጠየቃቸው ።

ወይዘሮ ጥሩነሽም ዱሮ ስንት እግር ነበረም ጌታ / ብለው ጠየቁት ።

እየጮኸ ቦት ጊዜ « ሁለት ሁለት ሁለት ነበረኝ አላቸው ።

ቦት ጊዜ ሁለት ስድስት ማለት ነው ። ልጅቷን ያሳደገች ላም ከራት እግር የበለጠ አልነበራትም ስለዚህ የእርስዎም እግሮች አራት ናቸው አሉት ።

« የምሬን ነው የምጠይቅም ? » አለና ጮሆ ተንዘረዘረ ።

በእርግጥ ሁለት እግሮች አሉዎት ጌታ አሉት ።

ተበጀ እግሩን እንኮንብሶ ለመሳም ሞከረና ራቀኝ ። ወደ ሰማይ እያየ መጠጥ ማለት ለእኔ ሞት ማለት ነው አለ ። ጊዜ ውም ሌሊት ነበር ።

እንደዚህ የማሉበት ሌሊት ያልፋል ብለው ወይዘሮ ጥሩነሽ መለሱለት ።


@gbw_dan
2015 e:c